1 አልሳም ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአስመጪነት የሚታወቅ የ 2015 በጀት ዓመት ገቢና ወጪ ከዚህ በታች አቅርቧል፡፡

- ሽያጭ--------------------------------------------------2,000,000
- ከውጭ አገር ያስመጣቸው ዕቃዎች ዋጋ ----------- ብር 827,887.50
- ደረሰኝ የቀረበላቸው አገር ውስጥ ግዢ ዋጋ……………….ብር 100,000
- ደረሰኝ ያልቀረበላቸው የተለያዩ ወጪዎች…………………. ብር 10,000
- ለቅጣት የተከፈለ --------------------------------------ብር 5,000
- የደመወዝ ወጪ ---------------------------------------ብር 40,000

  (ብር 10,000 ስራ ግብር ያልተከፈለበት ወጪ)
- ደረሰኝ ያልቀረበበት የመኪና ኪራይ ብሎ ያቀረበው ወጪ-- ብር 30,000
- ድርጅቱ ከተቋቋመበት ውጭ የተገኘ ገቢ ……………………. ብር 15,000
- የመዝናኛ ወጪ ………………………………………………….ብር 20,000

1. ግብር ከፋይ ባቀረበው ሒሳብ መዝገበ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ምን ያህል ነው
2. አልሳም ኃ/የተ/የግ/ማህበር በ 2015 ግብር ዘመን መክፈል ያለበት ንግድ ትርፍ ግብር ምን ያህል ነው?

2 ዳዲ ካምፓኒ የኪራይ ቤቱ እና የመኖሪያውቤቱ በአንድ የመብራት፣ የስልክ፣ የውሃቆጣሪ የሚጠቀም ሲሆን የመብራት ብር 5000 የውሃ 1200 ብር እና የስልክ 3000 ብር የክፍያ ቢል ያሳያል። ስለዚህ ዳዲ ካምፓኒ ለታክስ ዓላማ እንደ ወጪ መያዝ ያለበት በአጠቃላይ ስንትነው?

3 ሥራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለሠራተኛው የሚከፈል አበል ዘርዝር የጉዳት ደረጃውን መለካት የማይቻል ከሆነ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ስንት % ከገቢ ግብር ነፃ ይደረጋል

4 4. UV ካምፓኒ በወር ብር 12,000 የቤት ኪራይ እና የቤት ውስጥ ዕቃዎች በብር 10,000 ለንግድ አገልግሎት ቢያከራይ የቤቱንና የመሬት ታክስ ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ብር 5000 ቢከፍል

ሀ. ዓመታዊ የቤት ኪራይ ገቢው ምን ያህል ነው?

ለ. የሚከፍለው ግብርስ ስንት ነው? መሰብሰብ ያለበት ተጨማሪ እሴት ታክስ ወይስ ቲኦቲ?

5. እርጅና ቅናሽ ለማስላት መሠረት የሚሆነው ዋጋ አብራራ

6. ግብር ከፋይ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ የሚያወጣው ወጪ በገደብ እና ያለገደብ ተቀናሽ የሚሆንበት ሁኔታዎች ግለጽ?

7 በሥራው ቦታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው ፐርሰንት ምን ያክል እንደሆነ ግለጽ

8. ማንኛውም ግብር ከፋይ ብድር በሚወስድበት ጊዜ ወይም የዱቤ ግዥ በሚፈጽምበት ጊዜ የዕዳ መመዝገቢያ መዝገብ መያዝ ያለበት ሰነድ ነው ምን ምን ናቸው?

9. የሂሳብ መዝገብ መግለጫዎች ይዘቶች እነማን ናቸው?

**10.** የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዴት ነው የሚወሰነው?

11. ሆቴሎች፣በሬስቶራንቶች ወይም በሌሎች የምግብ አገልግሎት ስራ ላይ እና በማዕድን ማውጣትና ፍለጋ፣በማኑፋክቸሪንግ እና በግብርናና ሆርቲካልቸር ስራ ላይ ለተሰማሩ የመዝናኛ ወጪ ምን ያህል ፐርሰንት መያዝ ይችላል?

12 ለረጅም ጊዜ ከተደረገ ውል ጋር ተያይዞ ገቢ እና ወጪ አያያዝ እንዲሁም ግብር ከፋዩ ኪሳራ ቢያጋጥመው ኪሳራውን የሚያሸጋግረው በምን መልኩ ነው? አብራሩ

13. ጂ ኤም ኃ.የተ.የግ.ማ አንድ የንግድ ማእከል ተከራይቶ የሚያከራይ ሲሆን ከሚያከራየው አጠቃላይ የአመት ገቢው 1,200,000 ብር ነው። ለአንድ ዓመት ለዋና አከራዩ የሚከፍለው 800,000 ብር ነው። አከራዩ ገቢውን ለማግኘት ቤቱን ብር 150,000 ለፓርቲሽን 80,000 ደግሞ ለማስዋቢያ አውጥቷል።

ግብር የሚከፈልበት ገቢ አስሉ

- በዚህ ኪራይ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበሰባል ወይስ አይሰበሰብም ለምን
  ተርን ኦቨር ታክስ

14 ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተደረገ ስጦታ ተቀናሽ የሚፈቀደው መጠን ምን ያህል ነው?

15. ማንኛውም ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ ምን ያህል  የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል?

16. በባል/በሚስት ስም የተመዘገበ ህንጻ ለግለሰቦቹ ንግድ ስራ የዋለ እንደሆነ የእርጅና ተቀናሽ ሊፈቀደ የሚችለው  ምን ሲ□ላ ነው?

17.ግብር ከፋይ ህንጻ ለመገንባት ብድር የወሰደ እንደሆነ የህንፃው የወለድ ወጪ ተቀናሽ አያያዝን አብራሩ

17 የካፒታል ሀብት ሲተላለፍ የሚያዝ መረጃን ዘርዝር?

18 የማይሰበሰብ ዕዳ በተቀናሽነት የሚያዘው ምን ሲያሟላ ነው ?

19 አንድ ድርጅት በህይወት ዘመኑ ስንት ግዜ ያጋጠመውን ኪሳራ ማሸጋገር ይችላል?

21. የሂሳብ መዝገብ መግለጫዎች ይዘቶች እነማን ናቸው?

**22.** የንግድ ስራ ከተቋረጠ በኋላ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር እንዴት ነው የሚወሰነው?